በአሜሪካ ፍትህ ሚኒስቴር
የፌዴራል ምርመራ ቢሮ (ኤፍ.ቢ.አይ.)

# ለዛቻና እና ማስፈራሪያ ስጋቶች፤ የምላሽ አሰጣጥ መመሪያ

## በአካል የሚደረግ ዛቻ

**በአካል የሚደረግ ዛቻ የሚባለው ዛቻውን የሚያደርገው ሰው በቅርብ ርቀት ከመሆኑ የተነሳ አይቀሬ ለሆነ አደጋ የመጋለጥ ስጋት በሚኖርበት ወቅት ነው። ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ሶስት አማራጮች ይኖሩዎታል:**

1.**መሮጥ:** የማምለጫ መንገድ መለየት።ሊያዘገዩ የሚችሉ ማናቸውንምእቃዎች መጣል። ከተቻለ ሌሎችም እንዲያመልጡ መርዳት። ወዲያውኑ 911 ይደውሉ።
2. **መደበቅ:** ከስጋቱ እይታ ለመሰወር መደበቅ። በሮችን መቆለፍና መግቢያዎችን መዝጋት። የሞባይል ስልክን (ንዝረትን ጨምሮ) ድምጽ አልባ ማድረግ። የስጋቱ ሁኔታ እስኪያበቃ ድረስ በጸጥታ መቆየት።
3. **መፋለም:** ፍልሚያ መግጠም የመጨረሻ አማራጭ መሆን ያለበት እና ህይወት ለአይቀሬ አደጋ የተጋለጠ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ የሚወሰድ አማራጭ ነው። በተቻለ መጠን የስጋቱን ሁኔታ ለማክሸፍ መጣር። የተቻለውን ሁሉ አካላዊ ትንኮሳና ቁጣን በማቀናበር ማጥቃት።

**በአካል የሚደረግ የቃል ዛቻ የሚባለው ዛቻው የተቃጣበትን ሰው ወዲያውኑ አደጋ ውስጥ የማይጥል ወይም በሌላ ግዜ  ሊፈጸም የታቀደ የአደጋ ስጋት ሲኖር ነው።**

- የተባለውን ዛቻና ማስፈራርያ በተነገረበት መልኩ በትክክል መመዝገብ ወይም ድምጹን መቅረጽ።
- ማስፈራራት ወይም ዛቻውን ሰላደረገው ሰው በተቻለ መጠን ገላጭ ዝርዝሮችን መመዝገብ: ስም ፣ መልክ፣ የቆዳ ቀለም ፣ ጾታ ፣ ቁመት ፣ ክብደት፣ የጸጉር እና የአይን ቀለም፣ድምጽ ፣አለባበስ ወይም ሌላ ማንኛውም መለያ ባህርያት።
- ዛቻው እና ማስፈራርያውን ለሕግ አስከባሪ አካል ሪፖርት ማድረግ።.

## በስልክ የሚደረግ ዛቻ

**በስልክ የሚደረግ ዛቻ በስልክ ጥሪ አማካይነት የሚደረግ ዛቻ ነው። ስልኩን የሚደውለው ግለሰብ በቅርብ በመኖሩ ምክንያት ተቀባዩን ወይም ሌሎች ሰዎችን በአይቀሬነት ለአደጋ የሚያጋልጥ ሁኔታ ካልኖረ በስተቀር፣ ስለደዋዩ ግለሰብም ሆነ ስጋት ስለሚፈጥረው ሁኔታ የሚቻለውን ያህል ማስረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።**

- ስልኩን ሳይዘጉ በተረጋጋ ሁኔታ ማዳመጥ።
- በተቻለ መጠን ደዋዩ ንግግሩን ሳያቋርጥ እንዲቀጥል በማድረግ ስለስጋቱ ልዩ ባህሪ፤ ሰለእርግጠኝነቱና በስልክ ተቀባዩም ሆነ በሌሎች ላይ ሊያደርሰው ስለሚችለው አይቀሬ አደጋ መረጃ መሰብሰብ።
- የሚቻል ከሆነ ሌሎች በአቅራቢያ ያሉ ሰዎች ማዳመጥ እንዲችሉ ማድረግ እና ለሕግ አስከባሪ አካላት ስለሁኔታው ሪፖርት እንዲያደርጉ ምልክት መስጠት።.
- ማንኛውንም በስልኩ የኤሌክትሮኒክ ማሳያ መስኮት ላይ የሚታይ መረጃ መቅዳትና መያዝ።
- ዛቻው በተነገረበት ሁኔታ፤ በትክክል በጸሁፍ ማስፈር።.
- የሚቻል ከሆነ ጥሪውን ድምጽ መቅዳት።
- ስለ ዝርዝር ሁኔታው ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር ለመነጋገር ራስን ዝግጁ አድርጎ መቆየት።

## በኤሌክትሮኒክ መልእክት የሚደረግ ዛቻ

**በኤሌክትሮኒክ መልእክት የሚደረግ ዛቻ የሚባለው በቀጥታ መልእክት ፣ በኢሜይል፣ ወይም በማህበራዊ ድረ ገጾች በኩል የሚደረግ ዛቻ ነው። ግለሰቡ ለደረሰው ዛቻ ካልታዘዘ፤ ስውር ዛቻና መጥፎ መዘዞች የሚያስከትሉ አደጋዎች ይገጥሙታል የሚለውን ማስፈራሪያ ሊያካትት ይችላል።**

- ካልታወቁ ግለሰቦች የሚላኩ የኤሌክትሮኒክ መልእክቶችንም ሆነ የተያያዙ አባሪዎችን አለመክፈት።
- ካልታወቁ ወይም ካልተጠየቁ ግለሰቦች ጋር በማህበራዊ ድረ ገጽ ላይ አለመገናኘት።
- የደህንነት መጠበቅያ ግብአትዎ ከፍተኛ ጥበቃ ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ የተደራጀ መሆኑን ማረጋገጥ።

**በኤሌክትሮኒክ መልእክት ዛቻ ቢደርስብዎ:**

- በፎረንሲክ ምርመራ ጠቃሚ ዝርዝር መረጃ ሊገኝበት ስለሚችል መልእክቱን አይሰርዙት ።
- መልእክቱን ኮምፕዩተር ላይ ከፍተው መተው።.
- ወድያውኑ ለሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ።.
- የመልእክቱን ርእሰ ጉዳይ፣ቀን፣ እና ሰአት ማተም፣ ፎቶ ማንሳት፣ ወይም ቅጂ መውሰድ።
- ማንኛውንም ኤሌክትሮኒካዊ ማስረጃ ሳይነካካ ጠብቆ ማኖር።

## የበይነመረብ ጥቃቶች

**የበይነመረብ ጥቃት ኤሌክትሮኒክ ነክ መሳርያዎን አደጋ ላይ ሊጥል እና የግል መረጃዎችዎን ሊያጋልጥ ይችላል።**

- ጠንካራ የሆነ የይለፍ ቃል መጠቀምና ለተለያዩ ድረገጾች አንድ አይነት የይለፍ ቃል አለመጠቀም።
- ጸረ-ቫይረስ እና ጸረ-ማልዌር መተግበርያዎች እራሳቸውን በየጊዜው እንድያዘምኑ ማዘጋጀት።
- የኮምፒዩተርዎን ውስጣዊ አካላት ማዘመኛዎች፤ በተገኙበት ቅጽበት ወዲያውኑ መተግበር።
- ባለ ሁለት ደረጃ የማንነት ማረጋገጫ መግብያ መጠቀም።
- የመረጃ ቋትዎን ተመሳሳይ ቅጂ በየወቅቱ ማደራጀት እና ማስቀመጥ።

**የበይነመረብ ጥቃት ሰለባ ሆኜ ሊሆን ይችላል ብለው ከተጠራጠሩ:**

- የኮምፕዩተርዎን መዘወርያ ስርአቶች አለመሰረዝ ወይም አለመለወጥ።
- የባንክ ሂሳብዎን ከስርቆት ለመጠበቅ ደንበኛ ከሆኑበት የገንዘብ ተቋም ጋር ወድያውኑ ግንኙነት መፍጠር።
- የይለፍ ቃልዎን መቀየርና ሂሳብዎን ከአጠራጣሪ ግብይቶች መቆጣጠር።

***አይቀሬ የሆነ አካላዊ  ጉዳት ሊደርስብዎት የሚችልበት ሁኔታ ላይ ከሆኑ ወዲያውኑ 911 ይደውሉ።***

*ለስጋት የሚያበቃ ዛቻ ካጋጠምዎ  በአካባቢዎ ካለው የኤፍ.ቢ.አይ. የመስክ ቢሮ ጋር  በመገናኘት  ስጋትዎን ያሳውቁ። በየአካባቢው ያሉት የመስክ ቢሮዎች  ዝርዝር  በ www.fbi.gov ድረ ገጽ ላይ ይገኛል። በተጨማሪም  በስልክ 1800 CALLFBI (1-800-225-5324) በመደወል ወይም  www.fbi.gov/tips በመጠቀም መረጃውን መስጠት ይቻላል።*

*ከዚህም በላይ ማንነትዎን ሳይገልጹ በስልክ ወይም በኢንተርኔት መስመር  ጥቆማ ማድረግ ይችላሉ።*

**በአሜሪካ ፍትህ ሚኒስቴር**
የፌዴራል ምርመራ ቢሮ

# ለዛቻና እና ማስፈራሪያ ስጋቶች፤ የምላሽ አሰጣጥ መመሪያ

## ዛቻ ወይም ማስፈራራት ቢገጥመኝ ማንን ነው ማነጋገር ያለብኝ? የአካባቢውን ፖሊስ  ወይስ ኤፍ. ቢ. አይን?

- እርስዎም ሆኑ ሌሎች ላልተጠበቀ አካላዊ አደጋ የተጋለጡ ከሆነ ፣ ወድያውኑ 911 በመደወል በአካባቢዎ ለሚገኘው ፖሊስ ያስታውቁ።
- ከፌዴራላዊ ወንጀል ጋር የተዛመደ ዛቻ ከደረሰብዎት በአካባቢዎ የሚገኘውን የኤፍ.ቢ.አይ. የመስክ ቢሮ (የመስክ ቢሮዎች ዝርዝር www.fbi.gov ላይ ይገኛል) ፣ በስልክ 1-800-CALLFBI  (ወይም 1-800-225-5324) ወይም በwww.fbi.gov/tips አማካይነት ያግኙ። የውጭ ሃገር ወኪል በሆነ ግለሰብ፣ በተደራጀ የወንጀል ቡድን፣ ወይም በመንግስት ባለስልጣን፣ አማካይነት የሚቃጡ ዛቻዎች በፌዴራል ወንጀል ምሳሌነት የሚካተቱ ናቸው። የሚያቀርቡት ሪፖርት ማንነትዎን ሳይገልጹ በሚስጥር የሚከናወን ሊሆን ይችላል።
- ሁሉም ክስተቶች የኤፍ.ቢ.አይ.ን የምርመራ መመዘኛ ገደብ ያሟላሉ ማለት አይደለም። የፌዴራል ወንጀልን መስፈርት የማያሟላ ክስተት ሰለባ ከሆኑ፤ በአካባቢዎ ለሚገኝ የፖሊስ መምርያ ሁኔታውን ማሳወቅ ይኖርብዎት ይሆናል። የአካባቢና የክልል ግዛት ስልጣናት፤ አጠራጣሪ ወንጀሎችን የሚመረምሩበት የተለያዩ የመመዘኛ ገደቦች አሏቸው።

## በ ኤፍ. ቢ. አይ. ከሚደረግልኝ ቃለ መጠይቅ ምን መጠበቅ እችላለሁ?

- የኤፍ.ቢ. አይ. ተወካይ በኤፍ.ቢ.አይ. የመስክ ቢሮ ወይም በሌላ ቦታ ከእርስዎ ጋር ሊገኛኝ ይችላል።
- ኤፍ.ቢ.አይ. ስለጥፋተኛውና ስለደረሰብዎት ዛቻ ሁኔታ የተቻለውን ያህል ዝርዝር መረጃ ያቀርቡ ዘንድ ይጠይቅዎታል።
- ስጋቱን በሚመለከት የኤፍ.ቢ.አይ. ተወካይ ከእርስዎ ጋር በጉዳዩ ላይ ክትትል ለማድረግ ሊገኙ የሚችሉበትን አድራሻ መረጃ ይጠይቅዎታል።
- ኤፍ.ቢ.አይ. ማንነትዎን እና የጉዳዩን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ጥረት ያደርጋል።
- ተገቢ ሆኖ ከተገኘ የኤፍ.ቢ.አይ. የተጠቂዎች አማካሪ ባለሙያ መረጃ እና ድጋፍ ለመስጠት በቃለ ምልልሱ ወቅት ሊገኝ ይችላል፣ ወይም ከቃለ ምልልሱ በኋላ በስልክ ወይም በደብዳቤ ሊደርሱዎት ይችላሉ።

## ኤፍ.ቢ.አይ. አቤቱታን ተቀብሎ ምርመራ ለመጀመር ወይም ላለመጀመር  የሚጠቀምበት መመዘኛ ምንድነው?

- ኤፍ.ቢ.አይ. የአሜሪካንን የፌዴራል ሕግ የሚጥሱና በተጠቂውም ላይ ጉዳት ወይም አደጋ  ሊኖር  እንደሚችል የሚጠቁሙ ዛቻዎችን መመርመር ይችላል።
- የአሜሪካ መንግስት፤ ከዛቻ ጋር የተዛመዱ ክሶችን በግለሰቦች ላይ በፍርድ ቤት የማቅረብ ችሎታውና እና አቅሙ በአያሌ ምክኒያቶች፤ ማለትም: እንደ ማስረጃው ጥራት፣ ድርጊቱን የፈጸሙ ግለሰቦችን የመለየት ችሎታው፣ የተጎነጎነውን ሴራ መለየት መቻሉ፤ እና/ወይም ጥፋተኛ ግለሰቦችን በቁጥጥር  ስር ለማዋል መቻል እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዘ ነው።

## ኤፍ.ቢ.አይ. የምርመራ ሂደት ቢጀምር  ምን መጠበቅ እችላለሁ?

- ኤፍ.ቢ.አይ. የፌደራል ወንጀል ተፈጽሞ ሊሆን ይችላል ብሎ ካመነ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የኤፍ.ቢ.አይ. ልዩ ወኪሎች ምርመራውን ያካሂዳሉ። ከምርመራው ጋር በተያያዘ፤ ልዩ ወኪሎቹ ፤ ከእርስዎ ወይም ከሌሎች የዛቻው ሰለባዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግን ያካተተ ማስረጃ ያሰባስባሉ።
- ስለደረሰብዎት ዛቻ ያለፋበትን ሁኔታና ገጠመኞች በፌዴራል የፍርድ ሸንጎ አባላት ፊት ቀርበው እንዲያስረዱ ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኒታም ሊኖር ይችላል።
- ተገቢ የሆን ምርመራ ይጠናቀቃል። ሆኖም ምርመራውን ለማካሄድ ረዘም ያለ ግዜ ሊወስድ የሚችልና እርስዎም በጉዳዩ ላይ የተደረሰበትን የእለት ተእለት እድገት የሚመለከት መረጃ አይደርስዎትም። በምርመራው ሂደት የሚደረስባቸውን፤ እንደ እስር ወይም በወንጀሉ መከሰስን የመሳሰሉ አበይት ክስተቶች ሲኖሩ እንዲያውቁት ለማድረግ ማናቸውም ጥረት ይደረጋል። ኤፍ.ቢ.አይ. እንደነዚህ ያሉ መረጃዎች ለህዝብ ከመለቀቃቸው በፊት፤ የተቻለ ከሆነ በቅድሚያ ለእርስዎ ለማሳወቅ በቁርጠኝነት ይሰራል። ሆኖም ግን፤ ኤፍ ቢ አይ ምርመራውን ሊጎዱ የሚችሉ ወይም  የሕግ አስከባሪ አባላትን ለአደጋ የሚያጋልጡ  ስስ መረጃዎችን ላለማሰራጨት ሁልጊዜ መጠንቀቅ ይኖርበታል።
- የኤፍ.ቢ.አይ. የተጎጂዎች አማካሪ ባለሙያ ሰለባዎች ተብለው ለተለዩት  ተጎጂዎች ድጋፍ፤ መረጃና አስፈላጊ ቢሆን እገዛ የሚያደርጉ የአካባቢ ተቋሞችን ለማመላከት ዝግጁ ሆኖ ይጠብቃል።

***ምንም እንኳን ዛቻ  ወይም ማስፈራሪያ እንዴት እንደተቃጣብዎት ያቀረቡት ዝርዝር መረጃ  ለምርመራ የሚያበቃ ውጤት ባያመጣም፤ ኤፍ ቢ አይ ዛቻዎችን  መከታተልና አቅጣጫዎችንም መለየት እንዲችል በመርዳት  ለሌሎች ተጎጂዎች  ድጋፍ  እንዲያደርግ ያግዛዋል።***

*በየከተማውና  በክልሎች የሚገኙ የኤፍ.ቢ.አይ  የመስክ  ቢሮዎች  አድራሻ  በ WWW.FBI.GOV. ላይ  ይገኛል።  አይቀሬ  በሆነ ቅጽበታዊ አደጋ  ውስጥ ቢገኙ  911 ይደውሉ።*